# <u>የስድስተኛ ክፍል አማርኛ የሞዴል ፈተና መለማመጃ</u>

## <u>ጥያቄ አራት</u>

1. ሀሰትና እውነትን እየደባለቀ የሚናገር ሰውን ለመግለጽ የምንጠቀመው ፈሊጣዊ ንግግር

   ሀ) መልከ ጥፉ ለ) ተልባ

   ሐ) ሁለት ምላስ መ) ቅቤ ጠባሽ

2. የሱ ባህሪ ደግሞ ልክ **<u>እንደ ተልባ</u>** ነው ፡፡ የተሰመረበት ሃረግ ምንን ይገልፃል ?

   ሀ) የማይረጋ ወይም አቋም የሌለው ለ) ለስላሳ

   ሐ) ጣዕም የሌለው መ) ሁሉም

3. **<u>እኛ</u>** የሚለዉን ቅጥያ በመውሰድ አዲስ ቃል ሊመሰረትበት የሚችለው ቃል የቱ ነው ?

   ሀ) በር ለ) አናጺ ሐ) ወንድ መ) ተማሪ

4. በ ዐረፍተ ነገር ውስጥ ሰዋሰዋዊ ስህተት ከምን አንፃር ሊከሰት ይችላል?

   ሀ) በጾታ አለመስማማት ለ) በመድብ አለመስማማት

   ሐ) በባለቤትና ግስ አለመስማማት መ) ሁሉም

5. **<u>ከድጡ ወደማጡ</u>** የሚለው ንግግር ምንን ያመለክታል?

   ሀ) በደስታ ላይ ደስታ ለ) በጥጋብ ላይ ጥጋብ

   ሐ) ከችግር ወደ ባሰ ችግር መ) በእድገት ላይ እድገት

6. ማጣት አስጨነቀው እንደ ድሮ እማ **<u>እጅ ሰፊ</u>** ነበር ፡፡ ለተሰመረበት ፈሊጣዊ አነጋገር ተስማሚ የሆነው የቱ ነው ?

   ሀ) ቸር ለ) ለጋስ ሐ) አባካኝ መ) ሀ እና ለ

7. የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር በአህፅሮት ሲፃፍ ትክክለ የሆነው የቱ ነው ?

   ሀ) የኢ. መ. ማ ለ) ኢ. መም. ማ ሐ) ኢ.መ.ማ መ) ኢ. መምማ

8. የተውሶ ቋንቋ እና የሌላ ሰው ሃሳብ መሆኑን ለመግለጽ የምንጠቀምበት ስርዓተ ነጥብ፡

   ሀ) ትምህርተ ስላቅ ለ) ትምህርተ አንክሮ

   ሐ) ትምህርተ ጥቅስ መ) መልስ የለም

LIVEWORKSHEETS

9. ............ የምንለው የሰው ልጅ በህይወት ዘመኑ ሲኖር አወንታዊ እና አሉታዊ ተግባሮችን ሲያከናውን ነው ::

ሀ) ተውኔት ለ) አፈ ታሪክ

ሐ) የህይወት ታሪክ መ) ሁሉም

10. ከሚከተሉት መካከል ባህላዊ የዳኝነት ስርዓት ያልሆነው :

ሀ) እድር ለ) የሃገር ሽማግሌ

ሐ) ፍርድ ቤት መ) ሁሉም

11. **ሃቀኛ** ለሚለው ቃል ተቃራኒ የሆነው የቱ ነው ?

ሀ) ታማኝ ለ) ቃል አባይ ሐ) ሁነኛ መ) ሃ እና ለ

12. ወይ ጉድ ምን ዓይነት ጣጣ ነው በሚለው ዓ/ነገር ውስጥ መግባት ያለበት ስር ዓተ ነጥብ :

ሀ) ትምህርተ ጥቅስ ለ) ቃለ አጋኖ

ሐ) ትምህርተ አንክሮ መ) ለ እና ሐ

13. አባባ ከገበያ ሽንኩርት ቲማቲም ቃሪያ እና ጎመን ገዛ ::

: በሚለው ዓ/ነገር ውስጥ የሚገባው ስርዓተ ነጥብ:

ሀ) ነጠላ ሰረዝ ለ) ድርብ ሰረዝ ሐ) ጥያቄ ምልክት መ) ቃል አጋኖ

14. አሁንም አሁንም ትሳቅልኝ እሷ፣

**የውተት አረፋ** በመሰለው ጥርሷ

የተሰመረበት ቃል አውዳዊ ፍቺ:

ሀ) ችምችም ያለ ጥርስ ለ) የበለዘ ጥርስ

ሐ) በጣም ነጭ ጥርስ መ) ጉራማይሌ ጥርስ

15. አፍንጫዋ **ሰንደዶ** የመሰለ ነው :: የተሰመረባት ቃል ፍቺ

ሀ) ደፍጣጣ ለ) ቀጥ ያለ ሐ) ቀጭን መ) ሰፊ

16. ከሚከተሉት ውስጥ ኢርቱዕ የሆነው የቱ ነው ?

ሀ) ተመታ ለ) ተሰበረ ሐ) ተቀየረ መ) ሁሉም

17. ሆደ........... በክፍት ቦታው ሊገባ የሚችለው ድርብ ቃል:

ሀ) ባሻ ለ) ሰፊ ሐ) መራራ መ) ሀ እና ለ

LIVEWORKSHEETS

18. አግረ........... በክፍት ቦታው ሊገባ የሚችለው ድርብ ቃል፡

ሀ) ቀላል ለ) መንገድ ሐ) ኛ መ) ሀ እና ሐ

19. ሰው........... በክፍት ቦታው ሊገባ የሚችለው ድርብ ቃል፡

ሀ) ሰራሽ ለ) ኛ ሐ) ከንቱ መ) ሀ እና ሐ

20. ሆድና........... በክፍት ቦታው ሊገባ የሚችለው ድርብ ቃል፡

ሀ) አፍ ለ) ምግብ ሐ) ጀርባ መ) ስራ

21. ከሚከተሉት አረፍተ ነገሮች መካከል በግል አስተያየት ላይ የተመሰረተው የቱ ነው?

ሀ) ውሃ ከከፍተኛ ወደ ዝቅተኛ ቦታ ይፈሳል

ለ) ሙስና የእድገት ፀር ነው

ሐ) ቆሳሻ ሲሸተኝ ጉንፋን ይይዘኛል

መ) አብዛኛዎቹ የኢትዮጵያ ሀይቆች በስምጥ ሸለቆ ውስጥ ይገኛሉ

22. ከሚከተሉት አማራጮች መካከል የህይወት ታሪክ አፃፃፍ ቅደም ተከተልን የያዘው የትኛው ነው?

ሀ) የትውልድ ቦታና ዘመን፣ ያበረከተው አስተዋፅኦ አስተዳደግ እና የትምህርት ደረጃ፣ የግል አስተያየት የሞተ ከሆነ የሞተበት ጊዜ

ለ) የትውልድ ቦታና ዘመን የሞተ ከሆነ የሞተበት ዘመን ያበረከተው አስተዋፃኦ፣ አስተዳደግ እና የትምህርት ደረጃ ፣ የግል አስተያየት

ሐ) የትውልድ ቦታና ዘመን ፣ የሞተ ከሆነ የሞተበት ዘመን አስተዳደግ እና የትምህርት ደረጃ ፣ ያበረከተው አስተዋፃኦ የግል አስተያየት

መ) ያበረከተው አስተዋፃኦ፣ የሞተ ከሆነ የሞተበት ዘመን አስተዳደግ እና የትምህርት ደረጃ፣ የትውልድ ቦታና ዘመን ፣ የግል አስተያየት

23. መገርሳ ጥቁር የቆዳ ጫማ ገዝቶ መጣ፡፡ በሚለው ዐረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረበት ሐረግ ምን አይነት ሐረግ ነው?

ሀ) ግሳዊ ሃረግ ለ) ቅፅላዊ ሐረግ ሐ) መስተዋድዳዊ ሐረግ መ) ስማዊ ሐረግ

24. ከሚከተሉት አረፍተ ነገሮች መካከል ሶስተኛ መደብን፣ ተውሳከ ግስንና የትንቢት ጊዜን ያካተተው የትኛው ነው ?

ሀ) እነርሱ ለራሱ ጉብኝት እዚህ ይመርጣሉ ለ) አስመረት ዛሬ የምግቢያ ፈተና ተቀበለች

ሐ) አንተ ለንግዶች ምሳ እዚህ ቤት አሁን ታዘጋጃለህ መ) ባልቻ ትላንትና የሀገር ልብስ ከዚያ ሱቅ ገዛ

LIVEWORKSHEETS

25. **<u>እኔ እና አንተ እሱንና እሷን እንገጥማለን</u>** በሚለው ዓረፍተ ነገር ውስጥ የሁለተኛ መደብ፣ ነጠላ ቁጥር፣ ተባዕታይ ጾታ

የተገለፀው ተውላጠ ስም የትኛው ነው ?

ሀ) እኔ ለ) እሷ ሐ) አንተ መ) እሱ

26. ከሚከተሉት ቃላት መካከል ርቱዕ የሆነው የቱ ነው?

ሀ) ተሰራ ለ) ተመገበ ሐ) አነበበ መ) ሁሉም

ከሚከተሉት ቃላት መካከል ሳቢ የሆነው የቱ ነው ?

ሀ) በላ ለ) ዓፈ ሐ) አነበበ መ) ሁሉም

27. ከሚከተሉት አማራጮች መካከል የመስሪያ ቤት ደብዳቤ የሚያካትተው የቱ ነው ?

ሀ) ቀን ፣ቁጥር ለ) ማህተም፣ ግልባጭ

ሐ) የላኪና የተቀባይ አድራሻ መ) ሁሉም

28. እናቴ ለእኔ **<u>ዓርአያ</u>** በመሆን የሕይወትን መንገድ አሳይታኛለች፡፡ ለተሰመረበት ቃል ተመሳሳይ ፍቺ የሚሆነው:

ሀ) ሰው ለ) ምሳሌ ሐ) እናት መ) ሁሉም

29. አትሌት ደራርቱ ቱሉ **<u>ስመጥር</u>** አትሌት ነች ፡፡ ለተሰመረበት ቃል ተመሳሳይ ፍቺ የሚሆነው:

ሀ) ታዋቂ ለ) ጎበዝ ሐ) ሯጭ መ) መልስ የለም

30. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ ልዩ ነው ?

ሀ) ማነፅ ለ) ማቃናት ሐ) መግራት መ) ማፍረስ

31. ከሚከተሉት ውስጥ ጥምር ቃል የሆነው የቱ ነው?

ሀ) ቤተ መንግስት ለ) ብረት ድስት

ሐ) ምግባረ ሰናይ መ) ሁሉም

32. ከሚከተሉት ውስጥ ባለ ምዕላድ ቃል የሆነው :

ሀ) አስተማሪ ለ) መፅሀፎ ሐ) ቤቱ መ) ሁሉም

33. ሆ ይላል ገበሬ፣

ሆ ይላል ገበሬ፣

ድብ እያፈረሰ በሽልማ በሬ፡፡ በዚህ ግጥም ውስጥ **<u>ድብ</u>** ማለት ምን ማለት ነው ?

ሀ) አርከን ለ) ሰፊ መሬት ሐ) ወንዝ መ) መልስ የለም

LIVEWORKSHEETS

34. <u>**እረኛ**</u> ማለት ምን ማለት ነው ?

ሀ) ታጋሽ ለ) ጠባቂ ሐ) ገበሬ መ) ሁሉም

35. የተባበሩት መንግስታት ድርጅት በምህፃረ ቃል ሲፃፍ ፡

ሀ) የተ/ መ/ድ ለ) ተ/መ/ድ ሐ) መ/ድ/ተ መ) መልስ የለም

LIVEWORKSHEETS